# የ«ቃሌ ሲምፖዚየም» በአንድነት ፓርቲ
# መጋቢት 20 ቀን በኢምፔሪያል ሆቴል ይካሄዳል !

ከአወደ - ኢትዮጵያ

መጋቢት 16  2001

የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በደህንነት አባላት ከታሰሩ ሶስት ወራት ሊሆናቸዉ ጥቂት ቀናት ነዉ የቀሩት። በነዚህ ወራት ዉስጥ እስከአሁን  ድረስ ሁለት ሜትር በሁለት ሜትር ባለ የጨለማ ክፍል ዉስጥ በግፍና በጭካኔ ከመታሰራቸዉ ባሻገር፣ ሕገ መንግስታዊና ሰብዓዊ መብታቸዉ ተረግጦ፣ ጠበቃዎቻቸዉን፣ መንፈሳዊ አባቶቻቸዉን ፣ ሐኪሞችን እንዳያዩ ታግደዉና በሌሎች ነፍስን በገደሉ እስረኞች ያልታየ ትልቅ ኢሰብአዊ ግፍና ጭካኔ በሕወሃት ባለስልጣናት እየደረሰባቸዉ ነዉ።

የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የሊቀመንበራቸዉን መታሰር በተመለከተ፣ በተከታታይ የተለያዩ መግለጫዎችን የሰጡ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን ከምእራባዉያን አገሮች ዲፕሎማቶች ጋርም በመነጋገር፣ በወ/ት ብርቱከን ሚደቅሳ መፈታት ዙሪያ  ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ እንደሆነ በሰፊዉ ተዘግቧል።

በቅርቡ ከአሜሪካኑ አምባሳደር ዶናልድ ያማማቶ ጋር ባደረጉት ዉይይት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በአስቸኳይ ካልተፈቱ፣ የአንድነት ፓርቲ አባላት በየክልሎቹ እየደረሰባቸዉ ያለዉ ወከባ ካልቆመና ገዢው ፓርቲ በጡንቻና በጠመንጃ ኃይል የሕዝብን ፍቃድ ለማፈን የሚያደርግዉ ጸረ ዲሞክራሲያዊና ጸረ-ሕግ እንቅስቃሴዎች አቁሞ፣ የፖለቲካ ምህዳሩን ካላሰፈ፣ በመጪዉ ብሄራዊ ምርጫ መሳተፉ የማይታሰብ እንደሆነ ገልጸዉ፣ አገሪቷ በአጠቃላይ ወደ ከፉ ደረጃ እንደምትሄድ ማስጠንቀቃቸዉ ይታወሳል።

በወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ ላይ በደረሰዉ ግፍና በጠቅላላዉ በኢትዮጵያ እያሽቆለቆለ በመጣዉ የዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት ዙሪያ፣ ያለዉን ሁኔታ በሰፊዉና በጥልቀት ሕዝብ የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖረዉ ለማድረግም ታላቅ ሲምፖዚየም የአንድነት ፓርቲ አዘጋጅቷል።

ሲምፖዚየሙ በኢምፔሪያል ሆቴል  መጋቢት 20 ቀን 2001 የሚደረግ ሲሆን፣ ስብሰባዉን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ከአዲስ አበባ ምክር ቤት የሚያስፈልገዉ ፈቃድ መጠየቁንና መፈቀዱን ለማወቅ ችለናል።

በዚህ ሲምፖዚያም በፖለቲካዉ አንጻርና በሕግ አንጻር ሰፋ ያሉ ትንታኔዎች የሚሰጡ ሲሆን ፣ዶር መራራ ጉዲናና አቶ ስዬ አብርሃ ከፖለቲካዉ ጋር በተገናኘ ፣ ዶር ያዕቅብ ኃይለማሪያምና አቶ ዘነበ (ሁለቱም የሕግ ባለሞያዎች) ደግሞ ከሕግ አንጻር የመደረጉ ትንተናዎችን የሚያቀርቡ እንደሆነ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

በሲምፖዚየሙ የተጋበዙ በርካታ እንግዶችና ጋዜጠኖች የሚኖሩ ሲሆን ወደ አምስት መቶ የሚጠጉ የሲምፖዚየሙ ተካፋዮች በኢምፔሪያል ሆቴል ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር ኢንጂነር ግዛቸዉ ሽፈራዉ ለዘጋቢዎቻችን እንደገለጹት፣ ሲምፖዚየሙ በገዢዉ ፓርቲ እየተደረገ ያለዉን ግፍ ከተለየዩ ማእዘናት በቀረቡና መረጃዎች ላይ ባተኮረ

መልኩ ለማሳየት እንደሚሞከር አስረድተዉ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በተመለከተ «ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በኢትዮጵያ እየተፈጸመ ያለዉ ግፍና መከራ አመላካች ቀስት ናቸዉ» ሲሉ የወ/ት ብርቱካን በግፍ መታሰር በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳሩ እንደጠበበ፣ ዜጎች በግፍና በጭካኔ እንደሚታሰሩና ሕግ እየተረገጠ እንደሆነ በግልጽ የሚያመለክት ነዉ » በማለት ነበር የወ/ት ብርቱካ ሚደቅሳን ጉዳይ ለአንድነት ፓርቲ ቁልፍና አብይ ጉዳይ እንደሆነ ያስረገጡት።

ከሲምፖዚየሙ ጎን ለጎን፣ ወ/ት ብርቷን ሚደቅሳን በሚያሳዝንና በሚያሳፋር መልኩ ለሶስት ወራት በጨለማ ቤተ ዉስጥ እንዲታሰሩ መደረጉን ታሳቢ በማድርግ አሁንም አገዛዙ እኝህን ቆራጥ ታጋይ ሴትን ቢያስርም፣ ሕዝብ ከጎናቸዉ እንደሆነ ለማሳየት የሻማ ማብራት ስነስርዓት ይፈጸማል።

ከአዲስ አበባ የደረሰን ዘገባ እንዳመለከተዉ የሻማ ማብራቱ ስነስርዓትና ሲምፖዚየሙ « የቃሌ ሲምፖዚየም» እና «የቃሌ ሻማ ማብራት» የሚል ስያሜ በአንድነት አመራር አባላት ተሰጥቶታል።

የሕወሃት መንግስት በሲዊድን አገር ያደረግቱን ንግግር አጣሞ ክስ ባቀረበበትና ርካሽ ፕሮፖጋንዳ በሚቆጣጠራቸዉ የሕዝብ ሜዲያዎች ጠዋትና ማታ በሚረጭበት ወቅት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሐቁንና እዉነቱን ያወቅ ዘንድ «ቃሌ» በሚል አርእስት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጽሁፍ ማቅረባቸዉ ይታወሳል።